# የሙከራ ጥያቄ ሁለት

I. በ "ሀ" ረድፍ የተቀመጡትን በ "ለ" ረድፍ ከተቀመጡት ጋር በማዛመድ ትክክለኛውን ቁጥር በባዶ ቦታው ላይ ሙሉ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ካርታ- | ............... ኬንትሮስን እና ኬክሮስን በመጠቀም የሚገለፅ መገኛ |
| 2. አንጻራዊ መገኛ- | ............... በመስፈርት በተገኘ መረጃ የሚዘጋጅ ንድፍ/ፕላን |
| 3. ፍጹማዊ መገኛ- | ............... የአንድ ሰው ወይም ነገር ፍሰት ነው፡ |
| 4. ጂ.ፒ. ኤስ- | ................ የአቅጣጫ ማሳያ መተግበርያ |
| 5. ንድፍ ካርታ- | ............... የመሬትን ገጽታ ወይም በመሬት ገጽታ ላይ አንድ የተለየ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፍል የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ |
| 6. አቅጣጫ- | .............. በአካባቢ ከሚገኙ ነገሮች/አገሮች ጋር በማነጻጸር የሚገለፅ |

II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. በአፍሪካ ካርታ ላይ የኢትዮጵያን ፍፁማዊ መገኛን የሚገለፀው የቱ ነው ?

ሀ) ከ $12^0$ እስከ $18^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና ከ 36 22 ምስራቅ ኬንትሮስ

ለ) ከ $3^0$ - $15^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና ከ $33^0$ - $48^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

ሐ) ከ $12^0$ ሰሜን ኬክሮስ እና ከ $41^0$ - $51^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

መ) ከ $12^0$ 19 ሰሜን ኬክሮስ እና ከ $43^0$ - $44^0$ ምስራቅ ኬንትሮስ

LIVEWORKSHEETS

2. ኢትዮጵያን በስተሰሜን በኩል የሚያዋስናት የምስራቅ አፍሪካ ሀገር መን ይባላል ?

ሀ) ኬን ያ　　ለ) ጂቡቲ　　ሐ) ኤርትራ　　መ) ሶማሊያ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የአፍሪካ ቀንድ ሀገር ያልሆነው፡-

ሀ) ጂቡቲ　　ለ) ናይጀሪያ　　ሐ) ሶማሊያ　　መ) ኢትዮጵያ

4. ከሚከተሉት መተግበሪያዎች መካከል የአንድን አካባቢ የገበያ ፅር ለመፈለግ የምንጠቀምበት መተግበሪያ የቱ ነው ?

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጎግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) ኮምፓስ

5. ትራፊኮች የመኪና አሽከርካሪዎችን በምን ያህል ፍጥነት እንደሚያሽከረክሩና የሚነዱበትን ፍጥነት ለመቆጣጠር የሚያስችለው መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ጂፒኤስ　　ለ) ጎግል ኧርዝ　　ሐ) ጎግል ካርታ　　መ) አጉሊ መነፅር

6. ተመራማሪዎች ሩቅ ያሉ ቦታዎችን ለማየት፣ ለመመርመር እና ስለተለያዩ በሽታዎች መከሰት ትንበያ ለመስጠት ተሚጠቀሙበት መተግበሪያ ምን ይባላል?

ሀ) ጎግል ካርታ　　ለ) ጎግል ኧርዝ　　ሐ) ጂፒኤስ　　መ) ስቴቶስኮፕ

7. ከሚከተሉት ውስጥ አንፃራዊ መገኛን የማይገልፀው የቱ ነው ?

ሀ) ሰሜን　　ለ) ደቡብ　　ሐ) ምስራቅ　　መ) ኬንትሮስ

8. ከሚከተሉት ውስጥ በቋሚ መስመሮች መካከል ያለውን ማዕዘናዊ ርቀት ለመለካት የምንጠቀምበት የሃሳብ መስመር ምን ይባላል ?

ሀ) የኬክሮስ መስመር　　ለ) ሰያፍ መስመር

ሐ) የኬንትሮስ መስመር　　መ) ዝግዝግ መስመር

9. ከሚከተሉት ውስጥ የባህር በር ያለው ሃገር የቱ ነው ?

ሀ) ማላዊ　　ለ) ኢትዮጵያ　　ሐ) ሩዋንዳ　　መ) ማዳጋስካር

10. በካርታ ወይም በሉል ላይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ወይም በተቃራኒው የተሰመረ የሃሳብ መስመር ምን ይባላል?

ሀ) ግሪንዊች ሜሪዲያን　　ለ) ቋሚ መስመር

ሐ) የኬንትሮስ መስመር　　መ) የኬክሮስ መስመር

LIVEWORKSHEETS